## ፓኖራማ ቁጥር 80

### የትዝብት አድማስ

ጥቅምት 22 ቀን 2002 ዓም

## ሥርዓት ሕዝብን ካልመገበ
## ሕዝብ ሥርዓትን ይበላል

የረሀብተኞቹ ተክለ- ሰውነት ቆዳ የተወጠረባቸው አጽሞችን የያዘ ነው፡፡ዐይናቸው ተሰርጉዶ ጉንጫቸው ጎድጉዶ፥ ሆዳቸው ነትሯል፡፡ ይህ ስዕል፥ ለአምሳ ዓመታት ባላነሰ ዕድሜ ሲታይ የነበረው በሀገራችን በኢትዮጵያ ነበር፡፡ ይኸው አሁንም እንደገና ተከስቷል ፡፡ በ1965-66ና እና በ1976 ዓመተ ምህረቶች ረሀቡ ባስከተለብን አሰቃቂ ዕልቂት ምክንያት የማንኛውንም ሰብዓዊ ፍጡር ልብ የሰበረውን የተቆለለ አፅማችንን የተመለከተ መላው የዓለም ሕዝብ፥ ምርር ብሎ አዝኖ ፥ የተቻለውን ሁሉ ርዳታ አድርጎልናል ፡፡ አልቅሶልናል ፡፡ የሀዘን እንጉርጉሮና የሙዜቃ ሙሾ አስምቶልናል ፡፡ “ዊ አር ዘ-ዎርልድ ” በሚል የሙዚቃ ድግስ የዓለምን ሕዝብ ያስተባበረ የሀዘን ተካፋይነቱን ገልጾልናል ፡፡ ዕርዳታውንም አጉርፎልናል፡፡ የዓለም ትምህርት ቤቶች ህፃናት ሳይቀሩ ፥ ምሳቸውን ከአፋቸው እየነጠቁ ለኢትዮጵያ ህፃናት ልከዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት፥ረሀብን ከምድረ ኢትዮጵያ አስወግደን፥ራሳችንን መግበን ፥ በረሀባችን ጊዜ የደረሰልንን የዓለም ኅብረት ሰብ የአክብሮት ምስጋና የምናስተላልፍበት ወቅት በሆነ ነበር ፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ራሱን ችሎ በችግሩ ጊዜ የደረሰለትን የዓለም ኅብረተስብ ምስጋና ለማቅረብ የሚችል ውለታ ከፋይ ሕዝብ ነው መባል ነበረብን ፡፡ ያ መሆኑ ቀርቶ አዲስ ለመጣብን የረሃብ መዓት አሁንም እንደገና የምፅዋዕት እጃችንን ወደ ዓለም በመዘርጋት ላይ ነን ፡፡

ሰብዓዊ ክብሩን መጠበቅን ለሚሻ ማናኛው ሰው፥ ምጽዕዋትን ከመጠየቅ የበለጠ ሞራል ሰባሪ ኃይል አይኖርም፡፡ በዚህ አኳኋን ሲታይ፥ በችግር ምክንያት፥እንደ ሰው ፊት የሚፋጅ ግለት ጭራሽ መኖሩን እንጠራጠራለን፡፡ አብሶማ አንድ ሕዝብ በየአሥር ዓመቱ በረሃብ አለንጋ እየተገረፈ እንደ አሳት የሚፋጀውን የሰው ፊት እያየ መኖር ይከብደዋል ፡፡ ይህ ዕጣ ፋንታ በተደጋጋሚ የኛ ብሔራዊ መለያችን መሆኑ ያሳዝነናል፡፡ ያንገበግበናል፡፡ ዛሬም እንደ ትላንትናው፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ፥

“ አምላክ ረግሞናል ? ፈጣሪ አዝኖብናል ?
ጎረቤት ጠልቶናል? ዓለም ሰልችቶናል ?

ወንዞቹ ነጥፈዋል ? ሰማዩ ተደፍቶ መሬቱ ከዶናል?
አራሽ ገበሬ አልቆ ከንዱን ተንተርሏል ?
ኧረ እሪ በሉ !
ረሀብና ጠኔ ዛሬም መጥቶብናል ፡፡
ምፅዋዕት ጥየቃው ይኸው ብሶብናል፡፡ ”
እያለ አዲስ የሰቆቃ ድምፁን እያሰማ ይገኛል፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ የሚመጡት ሥርዓቶችን የሚያራምዱ ሁሉ ፥ ተቀዳሚ ተግባራቸውና ኃላፊነታቸው ዜጎችን መመገብ መሆኑን በጭራሽ አያምኑበትም ፡፡ ሁሉም በሥርዓተ- ዘመናቸው ሂደት ፥ ዜጎቹን መመገብ አለመቻለቻው ባቻ ሳይሆን ፥ መራባቸውንም እንኳ እንዲያውቁላቸው አይፈልጉም ፡፡ የወገንም ይሁን የውጭ ርዳታ እንዳይገኝ፥ የረሀቡን ክብደትና ብሶት እንዲገለጽ አያደርጉም፡፡ከዚህም አልፈው ተርፈው፥የአገዛዝ ሥርዓታቸውን ለማጠንከር በሚያደርጉት ከንቱ ሽርጉድ የሀገሪቱን ሀብት ለራሳቸው በዓል ማክበሪያና ፈንጠዝያ ያፈስሱታል ፡፡ በስድሳዎች ዓመታት ፥ ወገናችን የወሎና የትግራይ ሕዝብ በረሀብ እንደቅጥል በሚረግፈበት ጊዜ ፥ በወቅቱ የነበረው ሥርዓት ቁንጮ የልደት በዓላቸውን ለማክበር የተደገሰውን ግብር የተመለከተው የዓለም ሕዝብ የኢትዮጵያን መሪዎች ባኀርይና ተግባር ተመልክቶ ታዝቧል ፡፡አዝኗል ፡፡ ተቆጥቷልም ፡፡ ለዚህም ነበር ዓለም ለረሀብተኛው ወገናችን ልግስናውን ያጎረፈው ፡፡ ረሀብተኛ ሕዝቡን ያላበላው ያ ሥርዓትም ፥ በ1974 (1966) ሕዝባዊ አመፅ ተብልቶ ቀርቷል ፡፡ያን አሳዛኝ የወሎን ረሀብ ለፖለቲካ ፕሮፓጋንዳ ፍጆታ በመጠቀም ፥ ሥልጣን ላይ የወጡት የደርግ አባላትም፥በበኩላቸው በ1976 ዓም የተከሰተውን ረሃብ ከመጤፍ ሳይቆጥሩ ፥ ወደ ሥልጣን የመጡ በትን አሥረኛ ዓመት ለማክበርና ጨቋኝ ፓርቲያቸውን ለመመስረት በዓል በሚል ቁጥሩ በትክክል ያልተመዘገበ ሚሊዮን ብር ወጭ አድርገው አስረሽ ምችው ማለታቸውን መላው ዓለም እንደገና ታዝቧል የኢትዮጵያ ሕዝብ ፥ወቅቱን እየጠበቀ በሚመጣው የረሃብ አለንጋ በየጊዜው መገረፉ ብቻ ሳይሆን ፥ የተፈራራቂ ሥርዓት አራማጆች ጭካኔ ሰለባ እየሆነ እንዲቀጥልም ጭምር ተፈርዶበታል ፡፡ ይኸው ዛሬም ፥በ2002 ዓም ለሦስተኛ ጊዜ ለተመሳሳይ ረሀብ መጋለጡን ፥ መላው ዓለም እየታዘበ ይገኛል፡፡ምናልባት ዛሬ እኛ በተደጋጋሚ በደረሰብን ችግር ምክንያት ተገድደን ርዳታ ለመጠየቅ ባይሰለቸንም ፥የዓለም ሕዝብ ግን ርዳታ መስጠት አይሰለቸውም ማለት አንችልም ፡፡በተደጋጋሚ ችግር አስገዳጅነት ምክንያት ርዳታ መጠየቅ ላይሰለች ይችል ይሆናል ፥ረዳታ ሰጭው ግን ፥ በኢትዮጵያ የሚፈራረቁት ሥርዓቶች በሚፈጥሩት ችግር መንስዔ ፥ የኛን ረሀብ ለመከላት ሳይሰለቹ ርዳታቸውን ይቀጥላሉ ብለን መጠበቅ አይኖርብንም ፡፡

በዚህ ዓመት የተከሰተውን ረሃብ አስመልክቶ በዓለም ዙሪያ የሚገኙ ታላላቅ የዜና ምንጮች ፥የመገናኛ ብዙኃን ፥የኤሌክትሮኒክስ ዜና አውታሮች በሰፊው ናኝተውታል ። በአሀዝና በሰንጠረዥ የተደገፈ ማስረጃ እያቀረቡ በሰፊው ተችተውበታል ። እንዲያውም በአለፈው ሳምንት በዓለም ዙሪያ ከተነገሩት ዜናዎች መካከል በሀገራችን የተከሰተው ረሀብ የመጀመሪያውን ረድፍ ይዟል ።በወያኔ የዘረኛ ሥርዓት በአሁኑ ወቅት ከሰድስት እስከ ዘጠኝ ሚሊዮን ረሀብተኛ የኢትዮጵያ ሕዝብ አስቸኳይ የምግብ ርዳታ እንደሚያስፈለገው አስታወቀዋል ።ለረሃቡ መንስዔ ያው የተለመዱት ቃላት ማለትም፥ጦርነትና የዝናብ ዕጥረት እንደ ማጠየቂያ ሲጠቀሱ የቆዩ መሆናቸው ባይዘነጋም ፥ ስረ- መሠረቱ ግን የሥርዓቱ ብልሹነት መሆኑ የሚካድ አይደለም። ወያኔዎቹ፥ እንኳንስ ለማያስጨንቃቸው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ቀርቶ፥በስሙ እንታገልለታለን ሲሉት ለነበረው ለትግራይምሕዝብ ቢሆን፥ከራሳቸው ጥቅም በላይ እንደማያስቡለት ጫካ በነበሩበት ወቅት በተግባር አረጋግጠዋል ።በዚያን ወቅት በትግራይ ረሃብተኛ ሕዝብ ስም የተሰበሰበውን ርዳታ ሁሉ ለራሳቸው ድርጅት ጥቅምና አገልግሎት ሲያውሉት እንደነበር በታሪክ የተመዘገበ ብሔራዊ ወንጀል መሆኑ ከትግራይ ሕዝብ የተደበቀ አልነበረም ። በረሀብ አለንጋ ሲገረፍ የነበረውን የትግራይን ወጣት ለእርሱ ርዳታ የመጣለትን ምግብ ነጥቀው ወደ ድርጅታቸው ካልገባ፥እህል እንደማያገኝ በማስገደድ የጥይት ራት ሲያደርጉት እንደነበረም ከትግራይ ሕዝብ ኅሊና ሊፋቅ አይችልም ። የወያኔ መሪዎች፥ ለረሀብተኛው መርጃ የመጠውን ርዳታ ለብሄር ድርጅታቸው መገንቢያ ተጠቅመ ውበታል ። የሦስተኛው ዓለም ተብሎ በሚጠራው ክፍል የሚኖሩ አምባገነኖች፥ ለርዳታ የሚመጣውን እህልና መድህኒት ለፖለቲካቸው መጠቀሚያ መሳሪያ በማድረግ የግፍግፍ ወንጀል ስለሚፈጽሙ፥የወያኔ መሪዎችም ይህንን ቢያደርጉ አያስገርምም ። የወያኔን ዘረኛ ሥርዓት በመደገፍ ሲያሽሞነምኑት የነበሩት ሁሉ፥በአሁኑ ወቅት የመጣውን ረሀብ አላየነም አልሰማንም ማለት ስላልሆነላቸው ፥ ወያኔን እያጋላጡት ይገኛል ። የሀገሪቱ ኢኮኖሚ 11ከ መቶ አድጓል ሲሉላቸወም ነበር።ተጣድፎ ማመስገን በኋላ ለመንቀፍ ይቸግራል ቢባልም ፤ የወያኔ ጡት አባቶች ግን ወደዱም ጠሉ፥በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚደረገው ማነኛውም ወንጀል እና ጥፋት የወያኔን መሪዎች በኃላፊነት ሲጠየቁ፥ ዋስ ጠበቃ ሊሆኑላቸው አይችሉም ። ምክንያቱም ፥“ በአጋጣሚ ነፋስ ያበጠ ፊኛ በቀላል እሾህ እንደሚተነፍስ ” ሁሉ፥ በውጭ ኃይሎች ተባባሪነት የተቋቋመው የወያኔ ዘረኛ ሥርዓትም ፥ በኢትዮጵያ ሕዝብ ውሳኔ እንደሚገረሰስ ማንም ሊጠራጠር አይችልም ። የወያኔ ሥርዓት እስካለ ድረስ ግን ረሀቡና ጠኔው ይቀጥላል። የሕዝብ ዕልቂት፥ ስደትና ፍልሰትም ይባባሳል።

ኢትዮጵያ ሀገራችን፥ ከግማሽ ምዕተ-ዓመት ባላነሰ ዘመን ውስጥ ሦስት ታላላቅ አሰቃቂ ርሀብና ጠኔ በመፈራረቁ፥ በአያሌ ሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ አልቆባታል። በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ዜጋዋም ፈልሶባታል። ወደ ምዕራቡ ዓለም የተሰደደውን እንኳ ለጊዜው ቢተው፥

በኢትዮጵያ አኅራባች ሀገሮች በረሃቡ ምክንያት የተሰደደው ዜጋዋ ኑሮ እጅግ መሪር እንደሆነ ብዙ የዐይን ምስክሮች የሚመሰክሩት ሃቅ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ የረሀብና ጠኔ መፈራረቅን አስመልክቶ፥ በርካታ መጻሕፍት ተጽፈዋል ፡፡ስፍር ቁጥር የሌላቸው የጥናትና የምርምር ሰነዶች ቀርበዋል ፡፡የሀገር ውስጥ፥የአካባቢና የዓለም አቀፍ ስብሰባዎች፥ሰሚናሮች ተካሄደዋል ፡፡የመፍትሄ ኃሳቦችና ውሳኔዎች ተላልፈዋል ፡፡ የፖለቲካ ጠበብት ፥ የኢኮኖሚ ሊቃውንት፥የርሻና የአየር ጠባይ ተመራማሪዎች ፥ የውሀ ጥናትና የመስኖ አጠቃቀም ባለሚያዎች ሁሉ በየበኩላቸው፥ያጭር፥ የመካከለኛና የሩቅ ጊዜ መፍትሄዎችንና ዕቅዶችን አቅርበዋል ፡፡ ለዕቅዶቹና ለመፍትሄ ኃሳቦቹ ማስፈጸሚያ የሚሆን በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ መመደቡ በየጊዜው ተገልጿል ፡፡ይህ ሁሉ ተደርጎ ግን ረሀብና ጠኔ በፍጹም ሊለቀን አልቻለም፡፡ ለምን? ይህን ጥያቄ ለመመለስ ረዥም ምዕራፍ ጉዞ መንከላወት አይኖርብንም፡፡ ወቅቱን እየጠበቀ በተደጋጋሚ ለሚመጣብን ረሀብ መሠረታዊ ምክንያቱን ፈልገን ማግኘት ይኖርብናል ፡፡ ለሀገራችን ሁለንተናዊ ችግር፥ረሀቡንም ጨምሮ ፥ መሠረታዊው ምክንያት ያለው ከመንግሥት ሥርዓት ላይ ነው ፡፡ በሕዝብ የተመሰረተ ፥ለሕዝብ የቆመና አሳታፊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እስከሌለ ድረስ፥ብሔራዊ ችግሮቻችን ይወገዳሉ ማለት ዘበት ነው ፡፡ ሦስቱም ተፈራረቂ ሥርዓቶች የየራሳቸውን አምባገነናዊ ሥርዓቶች ተክለው ሀገርና ሕዝብ ጎድተዋል፡፡ ቀደም ሲሉ የነበሩት ሁለቱ ሥርዓቶች፥ ሕዝቡን ባለመመገባቸው ፥ በሕዝብ ተበልተዋል ፡፡ይህ የወቅቱ ዘረኛ ሥርዓትም ሕዝብን በርሀብ ስለሚጠብስ ፥ ጊዜው ሲደርስ እርሱም በበኩሉ፥ የጁን ያገኛል ፡፡ ይህ የታሪክ ሀቅ ነው፡፡ እስከዚያው ድረስ ግን ሥርዓቱን ለመለወጥ የሚታገለው፥ ትግሉን ይቀጥላል፡፡ ሕዝቡም ከረሀብ መቅሰፍት ሕይወቱን ለማዳን ይታገላል ፡፡ ከረሀብና ጭቆና ለአንዴም ለሁሌም ለመገላገል አምፆ መነሳት፣መታገልና የወያኔን አገዛዝ ማስወገድ ያሰፈልጋል ፡፡ በመሆኑም፥ ፀረ ወያኔ ትግላችን ከማፈፋም በቀር ሌላ ምርጫ ሊኖር አይችልም፡፡
የሕዝባችን የረሃብ ስቆቃ እምባ ያለቀሱ ብዙ ስማዕታት፣ደራሲያንና፥መዘምራን አልፈዋል፡፡

“ ዋይ! ዋይ! ዋይ! ሲሉ፥ የረሀብን ጉንፋን ሲስሉ፥
አስጨነቀኝ ጭንቀታቸው ፥ ምንስ ሆኜ ምን ላርጋቸው?”
እያለ ለቅሷቸውን አልቅሶ፣ ወደ እነሩሱው ዓለም ሄዷል ጥላሁን ገሠሠ !

ሎሬት ፀጋየ ገብረ ድኅንም በበኩሉ፥ ስለ ረሀብኞች ወገኖቹ ስቆቃና ጠኔ ተቀኝቷል፡፡ አዝኗል፡፡ በሕይወቱ ሳለ ሲመኘው የነበረውን የረሀብተኞቹን ጠግቦ መብላት በዓይኑ ሳያይ በስደት ዓለም እንዳዘነ ሞቷል ፡፡ የሀገራችን ረሀብና ጠኔም ቀጥሏል ፡፡ ሥርዓት ሕዝብን ካልመገበ፥ ሕዝብ ሥርዓቱን እንደሚበላ ግን የታሪክ ሀቅ ነው፡፡